# የታኮማ ፓርክ ከተማ፣ ሜሪላንድ

## የምርጫ ማሙያዎች

### የከንቲባ ዕጩ

ለከንቲባ ቢሮ እጩዎች በከተማው ከምርጫው ቀደም ብሎ ቢያንስ ለስድስት ወራት ነዋሪዎች መሆን ሲገባቸው፣ በምርጫው ቀን ቢያንስ 18 አመት እድሜ ሊኖራቸው ይገባል፤ እንዲሁም የከተማው ያሙዋሉ መራጮች መሆን አለባቸው። ከንቲባው በቢሮው ወቅት  ዋና ነዋሪነቱን በከተማው መቀጠል አለበት። ከንቲባው መኖሪያውን ከከተማው ከቀየረ፣ የከንቲባው ስራ ወዲያውኑ የሚቋረጥ ሲሆን፣ የሚፈጠረውም ክፍት ቦታ በከተማ ቻርተር አንቀጽ 308 በቀረበው መሰረት መሞላት ይኖርበታል። ከንቲባው በቢሮው ወቅት ሌላ የተመረጡ ቢሮዎችን ከመያዝ የተከለከለ ሲሆን፣ በማንኛውም የከተማ ቦርድ፣ ኮሚሽን፣ ወይም ሌላ ጉዳዮችን የመዝጋት ወይም የመፍታት ስልጣን ያለውን አካል ከማገልገል የተከለከለ ነው።

### የካውንስ አባል ዕጩ

የካውንስ አባል እጩዎች በከተማው (እና በሚመረጡበት ዋርድ) ከምርጫው ቀደም ብሎ ቢያንስ ለስድስት ወራት ነዋሪዎች መሆን ሲገባቸው፣ በምርጫው ቀን ቢያንስ 18 አመት እድሜ ሊኖራቸው ይገባል፤ እንዲሁም የከተማው ያሙዋሉ መራጮች መሆን አለባቸው። የካውንስ አባላት በቢሮው ወቅት የከተማ ዋና ነዋሪነታቸውን እና ዋርዳቸውን መቀጠል አለባቸው። የካውንስ አባል መኖሪያውን ከከተማው ወይም ከተመረጠበት ዋርዱ ከቀየረ፣ የካውንስ አባሉ ስራ ወዲያውኑ የሚቋረጥ ሲሆን፣ የሚፈጠረውም ክፍት ቦታ በከተማ ቻርተር አንቀጽ 308 በቀረበው መሰረት መሞላት ይኖርበታል። የካውንስ አባላቱ በቢሮው ወቅት ሌላ የተመረጡ ቢሮዎችን ከመያዝ የተከለከለ ሲሆን፣ በማንኛውም የከተማ ቦርድ፣ ኮሚሽን፣ ወይም ሌላ ጉዳዮችን የመዝጋት ወይም የመፍታት ስልጣን ያለውን አካል ከማገልገል የተከለከሉ ናቸው።

*የተከለሰ 2017-07-07*